# ማንነታችን በአደዋ

129ኛው የአደዋ ድል ክብረ በዓል በሜልቦርን

01–3–2025

ታጠቅ መንጂ

## ማንነት

የማንነት ውድድር ምክንያቶች ምንድን ናቸው ? የማንነት ውድድር መቼ ተጅመረ ?እንዴት ተጅመረ ?  ስንት ዓይነት ማንነቶች አሉ ? የሰው ልጅ ብቻ ነውን ለማንነት የሚወዳደረው ? ወዘተርፈ የተሰኙትን ጥያቄዎች መመለሱና መግለጹን ትቼ ፤ በእኔ እይታ አሁን ያለንበት ዓለም ሁለ-እንተናዊ እድገት- የማንነት ማስመስከርያ ውድድሮች ውጤት (ፕሮዳክት) ነው እላለሁ ። ብሄሮች/አገሮች ፣ አሁጉሮች ፣ግለሰዎች ፣ቡድኖች  ወዘተርፈ ለማንነት ይወዳደራሉ ።

- ማንነት - በጥንታዊ አገርነት፣የጥንታዊ ቅርሳ ቅርስ ባለቤት በመሆን
- ማንነት– በጥንታዊ ሥልጣኔ በመታወቅ
- ማንነት - በኢንዱስትሪ ፣ በቴክኖሎጂ ፣ በኮሚኒኬሽን ወዘተርፈ ሥልጣኔ
- ማንነት -  በንጥረ ነገሮች (በኬሚስትሪ)፣በመደሃኒት ቅመማ ቅመም ምርምር ለኖቬል ሽልማት በመብቃት
- ማንነት– በሃይል ምንጭ (በፊዚክስ)፣ በጠፈር ምርምር እውቅ በመሆን
- ማንነት - በሥነጽሁፍ ፣ በፍልስፍና ፣በማህበራዊ ሳይንስ ፣በኤኮኖሚክስ ሳይንስ ጥናቶች  እውቅና በማግኘት
- ማንነት - የዓለምን ሰላም በማስፈን ሥራ - የኖብል ሽልማት በመወሰድ
- ማንነት - በአለምፒክ በተለያዩ የስፖርት ግጥሚያዎች - የወርቅ ፣ የብርና የነሃስ መዳሊያ በማግኘት
- ማንነት–በመልካም/በዲሞክራሲያዊ አስተዳደር እና  ፍትህ በማስፈን ተምሳሌት በመሆን
- ማንነት– በሕዝባዊና ወታደራዊ ጀግንነት
- ማንነት– ከባዕዳን አገዛዝ ነጻ የሆነ  – ብሄራዊ ሉዓላዊነትን፣ታሪክን፣ ባህልን፣ ቋንቋን፣ እኔነትን ወዘተርፈ ሳያስደፍሩ እና  ሳያስነኩ በኩራት የመኖር ማንነት ።

- ብሄራዊ ሉዓላዊነት በቅኝ ገዢ ሥር ከወደቀ -በቅኝ ገዥዩና በቅኝ ተገዢዩ ሕዝብ መካከል የሚኖረው ግንኙነት - የባሬያና የጌታ ነው የሚሆነው ። ያንን ቀድመው የተረዱት አያቶቻችን ፤

  እናንተ ከእኛ በታች ናችሁ ፣ እኛን ለማገልገል እና  በእኛ እንድትገዙ ነው የተፈጠራችሁት ፣ሳትወዱ በግድ እንገዛቿኋለን ወዘተርፈ  በማለት በንቀትና በትምክህት ከአውሮፓ ወደ ኢትዮጵያ የገሰገሰውን የጣሊያን ሠራዊት በዚህ ቀን፤ በየካቲት 23/ 1888 ዓ.ም አደዋ ላይ በጀግኖች አያቶቻችን ድባቅ ተመታ ። ስለሆነም የማንነቶች ሁሉ ማንነት አጎናጽፈውን አልፏል፤የማንነቶች ሁሉ ማንነት ማማ ላይ አስቀምጠውን ተሰናበቱን

ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን፣ ነጭን በጥቁር ሰው እንደሚሸነፍ ለሞላው ዓለም ጥቁሮችን አስተምረው አልፈዋል ።

“በአደዋ ጦርነት የምኒሊክ ሠራዊት 40/100 የሚሆነው  የኢጣሊያን ሠራዊት ገድለዋል ፤ አቆሰለዋል ። ከጦርነቱ በኋላ የፈረንሳይና የእንግሊዝ ሉዕካን ወደ አዲስ አበባ ሄደው አጼ ምኒሊክ በአፍሪካም በአውሮፓም ከወቅቱ ሃያል መንግሥታት አንዱ መሆናቸውን እውቅና ሰጥቷቸው ተመለሱ” በማለት (ሪቻርድ ፓንክረስ) መሰከሯል።

“ኢትዮጵያውያን አርበኞች የማረከዋቸውን 1800 ኢጣሊያኖች- ስብዕና በተካሃነ ሁኔታ ተስተናግደው -ሁሉንም በሰላም ወደ አገራቸው ተመልሰዋል ፤ ያንን በጎ ሥራ - በምኒሊክና በአውሮፓውያን መካከል መልካም የዲፕሎማሲ ግንኙነት እንዲፈጠር ረቷል” በማለት (አቬዲዝ ቴራዚያ) መስክሯል ።

እ.አ.አ ከ1888 -1940 የኖረው -የራስተፈሪያን እምነት መሰረት የጣለውና የሞላ ዓለም ጥቁሮች መሻሻል ድረጅት (universal Negros Improvement Association) መሪ የነበረው ጃሜካዊው ማርከስ ጋርቪ - ከአደዋ ጦርነት በኋላ ፡-

“ሁሉንም ጥቁሮች በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት እንዲኮሩ፤ ኢትዮጵያ ሁሉንም ጥቁር ነጻ ታወጣለች፤ እኛ ጥቁሮች ተሰቃይተናል፣ ወደ ኢትዮጵያ መሄድ አለብን –back to home,back to Ethiopia” ወዘተርፈ እያለ ይሰብክ ፣ያስተምር ነበር ።

ኢትዮጵያ በጀግኖች ልጆቿ ታፍራና  ተከብራ ለዘላለም ትራለች!

በጀግኖች ልጆቿ ኢትዮጳዊ ስነልቦናና በተባበረ ክንዳቸው ሊያፈርሷት የተነሱትን የዛሬቹ አገር በቀል ባንዶች፤ ጉግ ማንጉጎችን ድባቅ ይመታሉ!